# የወጣት አገልግሎት ምንድ ነው?

## በአውስትራሊያ ውስጥ ስላለው የወጣት አገልግሎት ቤተሰብ በበለጠ ለማወቅ ሲፈልግ የወጣ መመሪያ

### መግቢያ

ይህ ትንሽ መጽሐፍ ወደ አውስትራሊያ ለመጡ ቤተሰቦች ተብሎ የወጣ ሲሆን ስለ የወጣት አገልግሎት ተግባራት በበለጠ እንዲረዳቸውና እንዴት ከወጣቶች ጋር መሥራት እንድሚችሉ ይረዳል።

አንዳንድ ሰዎች ስለ የወጣት ሠራተኛ ላይሰሙ ይችላሉ፣ ሌሎች ሰዎች ደግሞ ምን እንደሚሠሩ ላያውቁ ይችላሉ፣ ወይም ለልጆቻቸውና ለቤተሰባቸው እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ላያውቁ ይችላሉ። በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ ያለው መረጃ በአውስትራሊያ ስለ የወጣት ሠራተኞች ጠቀሜታና የወጣት አገልግሎት ቤተሰቡ በበለጠ እንዲያውቅ ይረዳል።

### ‘ወጣት’ የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?

ወጣት ስለሚለው ቃል እያንዳንዱ ባህል ለየት ያለ የአተረጓጎም ሃሳብ ሲኖረው ወጣቶች በሚያድጉበት ጊዜ በቤተሰብ ውስጥና በማህበረሰብ ውስጥ መሆን እንዳለባቸው ተገቢ ነው።

በአጠቃላይ በአውስትራሊያ ውስጥ እድሚያቸው ከ12 እስከ 25 ዓመት ባለው ጊዜ ‘ወጣት’ ይባላል። አንዳንድ ጊዜ እድሚያቸው ከ12 እስከ 18 ዓመት የሆኑ ‘ጎረምሳ/ኮረዳ’ ሲባል እንዲሁም እድሚያቸው ከ21 እስከ 25 ዓመት የሆኑ ‘የወጣት አዋቂ’ ይባላል። ከህጻንነት እስከ አዋቂ ሰው መሆን ያለውን የተለያየ ደረጃ ለመግለጽ እነዚህ ቃላትን እንጠቀማለን።

‘ለወጣት’ አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች ወይም እንቅስቃሴዎች በተለይ እድሚያቸው ከ12 እስከ 25 ዓመት ለሆኑ ወጣቶች የሚቀርብ ይሆናል።




### የወጣት ሠራተኛ ማን ነው?

በአውስትራሊያ ውስጥ ያሉት የወጣት ሠራተኞች ወጣቶችን ለመርዳት ልምድና ችሎታ ያላቸው ሲሆኑ ደህንነቱ የተጠበቀ የሚያዝናና እንቅስቃሴ ያቀርባሉ። ‘ለተቸገሩ’ ወጣቶችና ቤተሰቦች ብቻ አይደሉም።

የወጣት ሠራተኞች ሌላ የመጠሪያ አርእስቶች ሲኖሩት ማለት እንደ ‘አማካሪ’፣ ‘የወጣት ጤና ሠራተኛ’፣ ‘የማሕበራዊ ሠራተኛ’ ወይም ‘የማህበረሰብ ልማት ሠራተኛን’ ያካተተ ይሆናል።

### የወጣት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ምንድ ናቸው?

በአውስትራሊያ ውስጥ ቤተሰብንና ወጣቶችን የሚረዱ ብዙ ድርጅቶች አሉ። ወጣቶችን በተለይ ለመርዳት አንዳንዶቹ የወጣት ሠራተኛ ይቀጥራሉ።

ለወጣቶች የተለየ አገልግሎቶች ወይም ፕሮግራሞች በሚከተሉት ሊቀርቡ ይችላሉ:

- በት/ቤት ወይም በቴፍ/TAFE
- በአካባቢ ምክር ቤቶች
- ቤተክርስቲያን፣ መስጊድ፣ ቤተመቅደስ ወይም በሌላ መጸለያ ቦታዎች
- ማይግራንት/ስደተኛ አገልግሎት (ለምሳሌ በማይግራንት መገልገያ ማእከላት)
- በማህበረሰብ የጤና ጥበቃ ማእከላት
- በማህበረሰብ ማእከላት
- በማህበረሰብ ህጋዊ የሆነ አቅራቢ ማእከላት
- በወጣት መጠለያ ቤት አገልግሎቶች
- በሠራተኛና አሠሪ አገልግሎቶች
- በአካለጎደሎ አገልግሎቶች

### የወጣት አገልግሎት ለምንድ ነው ያለው?

እድሚያቸው ከ12 እስከ 25 ዓመት ባለው ጊዜ ወጣቶች ከልጅነት አዋቂ እስከሚሆኑ ድረስ ብዙ የእድገት ደረጃዎች ያሳያሉ። በነዚህ ዓመታት ውስጥ የወጣቶች ፍላጎት እንደ ህጻናት ወይም አዋቂ ሰው ባለመሆኑ ታዲያ ተጨማሪ እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። በተለይ ይህ እርዳታ በቅርቡ ወደ አውስትራሊያ ለመጡ ወጣቶች ይሆናል። ብዙ ወጣቶች በቤታቸው የሚያጋጥማቸውንና ከጓደኞቻቸው ወይም ከት/ቤት የሚያገኙትን አዛምዶ ሚዛናዊ ግምት መውሰድ ያስቸግራቸዋል። ብዙጊዜ ብቸኝነት ሊሰማቸው ይችላል እንዲሁም ቀደም ሲል ምን እንዳጋጠማቸው ማንም አይረዳላቸውም።

cmyi centre for multicultural youth issues

## የወጣት አገልግሎቶችና የወጣት ሠራተኞች ጠቃሚነቱ ለምንድ ነው?

ወጣቶችንና ቤተሰቦችን ለመርዳት የወጣት አገልግሎትና ሠራተኞች ይገኛል። በአውስትራሊያ ኑሮን ለማስተካከል አስቸጋሪ ሊሆን ሲችል እንዲሁም በአዲስ ቋንቋና የተለየ የአኗኗር ዘዴ ባለበት ስለአዲስ የትምህርት፣ የሥራና የጤና ጥበቃ አሠራር ዘዴ መነጋገሩ አስቸጋሪ ሊሆን ይሆናል።

ለአውስትራሊያ አዲስ የሆኑ ቤተሰቦች ካላቸው አንዳንድ ልምዶች የሚከተሉትን ያካትታል:

- ልጆችዎ እቤት ከሚቆዩ በበለጠ ከጓደኞቻቸው ጋር ጊዜ እንዲያጠፉ ይፈልጋሉ;
- ለልጅችዎ ምን እንደሚጠበቅ ለየት ያለ ሃሳብ ይኖርዎታል፣ ለምሳሌ ስለዝምድና ወይም ጋብቻ መፈጸም;
- በቤተሰቡ አዲስ ጋብቻ በመፈጸሙና በሌላ ምክንያት ከተለያዩ በኃላ እንደገና እውቅና መፍጠር;
- የወጣት ሠራተኞች ከነዚህ አንዳንድ ጉዳዮች ጋር በተዛመደ ወጣቶችንና ቤተሰብን መርዳት ይችላሉ። መርዳት ካልቻሉ ብዙጊዜ መርዳት የሚችል ሰው ፈልገው ያገናኛሉ።

ስለ ገንዘብ ወይም ት/ቤት መሄድ ወይም ሥራ መፈለግ ጉዳይ ተቃውሞ ይኖርዎታል።

## በወጣት ፐሮግራሞችና አገልግሎቶች መካከል ምን አይነት ልዩነቶች አሉ?

ለወጣቶች ብዙ አይነት የወጣት ፐሮግራሞችና አገልግሎቶች ይኖራሉ። የወጣት ፐሮግራሞች ብዙጊዜ ወጣቶች በቡድን እንቅስቃሴ ተሳትፎ ለማድረግ የሚሰበሰቡበት ይሆናል።

ከፐሮግራሞቹ ወይም እንቅስቃሴዎቹ አንዳንድ ምሳሌዎች የሚከተሉት ይካተታሉ:

- የቤት ሥራ ቡድን ወይም ክለብ (ለምሳሌ፡ ከት/ቤት ሥራ ጋር በተዛመደ በዩኒቨርስቲ መምህር/ቱቶር እርዳታ ማግኘት)
- የሥራና አሠሪ ፐሮግራሞች (ለምሳሌ፡ የሚከፈልበት ሥራ ወይም ለሥራ ልምድ ለማፈላለግ የህይወት ታሪክን በጽሁፍ ማዘጋጀት/ resume or CV)
- ከትምህርት በኃላ እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ፡ ስፖርት ወይም የጌጣጌጥ ሥራ)
- የመዝናኛ ፐሮግራሞች (ለምሳሌ፡ ባህላዊ ወይም ዘመን አመጣሽ ዳንስ እስክስታ)
- የስፖርት ፐሮግራሞች (ለምሳሌ፡ ባስኬትቦል፣ የእግር ኳስ፣ ዋና)
- በት/ቤት እረፍት እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ፡ ሲኒማ ለማየት መሄድ፣ የዱር አራዊት እንስሳትን መጎብኘት፣ ወይም በእረፍት የሰፈራ/ካምፕ መሄድ)
- አመራር፣ መካሪ መሆንን እና ሌሎች የስልጠና ፐሮግራሞች (ለምሳሌ፡ በአደባባይ የመናገር ችሎታ ትምህርት)
- የወጣት ቡድን ፐሮግራሞች (ለምሳሌ፡ በራስ መተማመን፣ ማንነትንና ባህልን ማጠናከር)

## ሱልታን/Sultan

ሱልታን ወደ አውስትራሊያ የተሰደደች ሲሆን በት/ቤት አንድ የወጣት ሠራተኛ ተማሪዋን ለመርዳት ጠየቃት። ተማሪዋ በክፍል መቅረት ስትጀምር አስተማሪዎች ስለእሷ ይጨነቁ ነበር።

የወጣት ሠራተኛው ከሱልታን ጋር ከተገናኙ በኃላ እሷ በአውስትራሊያ ኑሮ እንደከበዳት አወቁ ታዲያ ለት/ቤት መጽሐፍት ለመግዛት እርዳታ እንደሚያስፈልጋትና የቤት ሥራን ለማካሄድ እንደከበዳት ነው። ስለዚህ የወጣት ሠራተኛው በት/ቤት ባለ የቤት ሥራ ክለብ በየሳምንቱ እንድትሄድ ሃሳብ ሲቀርብ እንዲሁም ለት/ቤት መጽሐፍት መግዣ እርዳታ እንደሚያስፈልጋት ጠቁሟል።

የሱልታን ቤተሰብ እሷን በወጣት ሠራተኛ ስለማየት ጉዳይ እንዲሁም ከት/ቤት ሰዓት ውጪ ባለ እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ እርግጠኛ አልነበሩም፣ ምክንያቱም ሱልታን በየትኛው የቤት ሥራ ቡድን እንደምትመደብ ስላላወቁ። ከወጣት ሠራተኛ ጋር ተገናኝተው ያላቸውን አሳሳቢ ጉዳይ ለማካፈል ቻሉ። በወጣት ሠራተኛ የሚቀርበውን በተሻለ ካወቁ በኃላ፣ የቤት ሥራ ቡድንን በመጎብኘት ምን እንደሚደረግ ካዩ በኃላ ሱልታን መሄድ እንደምትችል ተስማምተዋል።

ሱልታን ሁልጊዜ በቤት ሥራ ቡድን ስለሄደች በት/ቤቷ የምትሠራው በመሻሻል ወደ ትምህርቷ ያለማቋረጥ ትሄዳለች።





 © Centre for Multicultural Youth Issues 2006



## የወጣት ድጋፍ መስጫ ፕሮግራሞች ምንድ ናቸው?

ይህ ፕሮግራም ብዙጊዜ ግላዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ነብስወከፍ የሆነ ድጋፍ ያቀርባል። በነዚህ ፕሮግራሞች በኩል ወጣቶችና ቤተሰቦች በተለያዩ ነገሮች ላይ እንደሚከተለው እርዳታ ማግኘት ይችላሉ:

- ተግባራዊ እርዳታ (ለምሳሌ፥ ቅጾችን መሙላት፣ ለትምህርት ማስመዝገብ፣ ቀጠሮ ማስያዝ ወይም ለት/ቤት መማሪያ መጽሐፍት ማግኘት)
- ለወጣቶችና ቤተሰባቸው አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ስለሚኖራቸው አማራጭ መረጃ ማቅረብ (ለምሳሌ፥ ባህላዊ የሆኑ ጉዳዮች)
- በቤተሰብ፣ ጓደኞች ወይም ት/ቤት መካከል ዝምድናን ለማጠናከር መርዳት (ለምሳሌ፥ በቤተሰብ መካከል ግንኙነትን ማሻሻል)
- ስለሌሎች አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች ወይም እንቅስቃሴ መረጃ በማቅረብ እርዳታ ማግኘት (ለምሳሌ፥ ህግን በተመለከተ መረጃ፣ ሐኪም ማግኘት ወይም ስለማይግሬሽን መረጃ አቅርቦት)
- ለችግሮች መፍትሄ ስለመፈለግ የሆነ ሰው ማነጋገር - አንዳንድ ጊዜ 'መማከርት' ተብሎ ይጠራል።

## የወጣት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ለሁሉም ወጣቶች ይቀርባልን?

አብዛኛው የወጣት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ለየት ላሉ የወጣት ቡድኖች ይቀርባል። ለምሳሌ፥ አንዳንዶቹ ምናልባት:

- ለልጃገረዶች ወይም ለወንድ ልጆች ብቻ (ለምሳሌ፥ ለልጃገረድ ዋና ወይም ለወንድ ልጅ የእግር ኳስ)
- በተወሰነ የእድሜ ክልል ላለ ቡድን (ለምሳሌ፥ እድሜው ከ15 እስከ18 ዓመት ወይም ከ18 እስከ 21 ዓመት ላሉ)
- በተለየ ሰፈርና አካባቢ ለሚኖሩ፣ ለሚሠሩ ወይም ለሚማሩ ወጣቶች።
- ከተለየ ባህላዊና ቋንቋ ከሚናገር ለመጡ ወጣቶች (ለምሳሌ፥ አረብኛ የሚናገሩ የልጃገረዶች ስብስብ ወይም የሕብረ ባህላዊ ስብስብ)
- 'ከክፍያ ነጻ' ይህ ማለት ሌሎቹ የተወሰነ ሲከፍሉ እርስዎ ግን ምንም ገንዘብ አይከፍሉም።
- በተለዩ ጉዳዮች ላይ ብቻ ድጋፍ ይቀርባል (ለምሳሌ፥ ከጤና ጋር በተዛመደ ችግር መርዳት)

እድሚያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶች ብዛት ባላቸው ፕሮግራሞች ውስጥ ከመሳተፋቸው በፊት ከወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ፈቃድ ማግኘት አለባቸው።

## በወጣት እንቅስቃሴዎችና ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ ጥቅሞቹ ምንድ ናቸው?

በወጣት ፕሮግራሞች፣ እንቅስቃሴዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ በመሳተፍ የሚገኙ አንዳንድ ጥቅሞች:

- ከትምህርት፣ ጤና እና ሥራ ጋር በተዛመደ ተግባራዊ የሆነ እርዳታ ማግኘት
- አዲስ ችሎታን መማር (ለምሳሌ፥ የእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ ስፖርት፣ በአደባባይ መናገር)
- ጓደኞች ማፍራት
- ስለ ሌሎች አገልግሎቱ ማብራሪያ ማግኘት (ለምሳሌ፥ የትምህርት ጤና ወይም ሥራ)
- ድጋፍ ማግኘት - ወጣቶች በራሳቸው እንዲተማመኑ እና ከቤተሰባቸው፣ ከጓደኞችና ማህበረሰብ ጋር ጠንከር ያለ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ብዙጊዜ ይረዳቸዋል።

ማንኛውም ሰው በራሱ ማህበረስብ ስለሚኖሩት አቅርቦት ለመጠቀም ሙሉ በሙሉ የመሳተፍ መብት ይኖረዋል። ወጣቶችና ቤተሰባቸው ይህንን ለማድረግ በወጣት ሠራተኛና አገልግሎት በኩል እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

## ልጆቼ በወጣት እንቅስቃሴ ወይም ፕሮግራም ውስጥ ሲሳተፉ ምን አይነት ግምት መውሰድ እችላለሁ?

የወጣት አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች ወይም እንቅስቃሴዎች በሞላ ደህንነታቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባዎታል። በተጨማሪም ከየትም ባህል ይምጣ ነገር ግን ለወጣቶች አወንታዊ የሆነ አካባቢ እንዳለ መገመት ያስፈልጋል።

### ለእንክብካቤ የሃላፊነት ግዴታ /Duty of Care

እንደ ማንኛውም አስተማሪዎች ወይም ሐኪሞች የወጣት ሠራተኞችም በፕሮግራሙ ወይም በእንቅስቃሴው ላይ ተሳትፎ ላላቸው ወጣቶች ለመንከባከብ ሃላፊነት እንዳለባቸው ሲሆን - ድህንነቱ የተጠበቀ ተሳትፎ ቅድሚያ ይሰጠዋል። ይህም 'ለእንክብካቤ የሃላፊነት ግዴታ' ተብሎ ይጠራል።

### ሚስጢራዊ/Confidentiality

የወጣት ሠራተኞች 'ሚስጢርን' በአግባቡ ለመያዝ ሃላፊነት አለባቸው። ይህ ማለት ለወጣት ሠራተኛ የተሰጠ ማንኛውም የግላዊ መረጃ በግል ይጠበቃል። የወጣት ሠራተኛ በወላጅ ወይም በወጣቱ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ስለ ግላዊ የሆኑ መረጃዎች ከሌሎች ጋር መነጋገር አይችሉም። ነገር ግን በድንገተኛ ችግር ጊዜ ለግለሰቡ ደህንነት ሲባል ያሉትን መረጃዎች ማካፈል ያስፈልጋል። 'ሚስጢራዊነትን መያዝ' ወይም ማክበር፣ ይህ ማለት ሰዎች ስለሌላ ሰው መረጃ ሳይጠይቁ ያላቸውን መረጃ ለማካፈል መተማመን እንዲችሉ ይሆናል።


© Centre for Multicultural Youth Issues 2006

## ጥያቄዎችና አሳሳቢ ጉዳዮች ካሉኝ ምን ማድረግ እችላለሁ?

የወጣት ሠራተኞች ስለሚኖራቸው ፕሮግራሞች ወይም አገልግሎቶች መረጃ ለርስዎ የማቅረብ ኃላፊነት ሲኖራቸው እንዲሁም ስለሚኖርዎ ማንኛውም አሳሳቢ ጉዳዮች ገለጻ ለማድረግ ኃላፊነት አላቸው። ልጅዎ በሚሳተፍበት ስለማንኛውም የወጣት ፕሮግራሞች ወይም አገልግሎቶች ላይ ጥያቄ ካለዎ መጠየቁ አስፈላጊ ነው። ከሁሉም ባህል የተውጣጡ ቤተሰቦች ወጣት የቤተሰብ አባላት ከቤታቸው ሲወጡ የትና ከማን ጋር እንደሚውሉ በማሰብ ይጨነቃሉ። ቤተሰብ ልጆቻቸው ደስተኛና ደህንነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን ማረጋገጡ የተለመደ ጉዳዩ ነው።

### ኳኢ/Qi

Qi የ16 ዓመት ጎልማሳና በቤቱ ችግር ያለበት ሰው ነው። ሁልጊዜ ከአባቱ ጋር ይጨቃጨቃል ምክንያቱም Qi ቅዳሜና እሁድ ከቤቱ መውጣት ስለሚፈልግና በራሱ ባንክ አካውንት ገንዘብ እንዲኖረው ስለሚፈልግ ነው። ስለዚህ ጉዳይ አባቱ ደስተኛ አልነበረም፣ እንዲሁም ከመጥፎ ልምድ ካላቸው ሰዎች ጋር ይገናኛል በሚል ይጨነቅ ስለነበር ነው።

Qi በት/ቤቱ አጠገብ ባለ የወጣት ሠራተኛ በመሄድ በበለጠ ነጻነት ማግኘት ወደሚችልበት ቤት መልቀቅ እንደሚፈልግ ተናገረ። የወጣት ሠራተኛው በቤቱ ውስጥ ምን እንዳጋጠመው በመጠየቅ ያለውን ዝምድና ማሻሻል የሚቻልበትን መንገድ ለመፈለግ ቤተሰቡን እንዲያነጋግር ፈቃድ ተጠየቀ።

ኣባቱ ከሠራተኛው የስልክ ጥሪ ሲደርሰው ከቤተሰብ ውጭ ያለ ሰው ከልጁ ጋር ያለው ችግር ስለታወቀ ሃፍረት ተሰማው። ለሎች የቻይና ማህበረሰብ አባላት ከሰሙ ምን ይላሉ በማለት ተጨነቀ። በተጨማሪም የወጣት ሠራተኛው ልጁ ከቤት እንዲወጣ ይገፋፋል በሚል ተጨነቀ። ነገር ግን ምን እንደተፈጠረ ከሠራተኛው ጋር ለመነጋገርና በስብሰባ ተገኝቶ መወያየት እንደሚፈልግ ወሰነ።

አስተርጓሚ በወጣት ሠራተኛው በኩል ተቀናጀ ከዚያ አባትና ልጅ አብረው እንዲነጋገሩ አበረታታ። በአውስትራሊያ ውስጥ ብዛት ያለው ቤተሰብ ችግር እንደሚያጋጥማቸው በሠራተኛው ማብራሪያ በመስጠቱ፣ ሁሉም ችግራቸውን ለመወያየት ዝግጁ በመሆናቸው የሚደነቅ ነው። Qi በቤት ውስጥ እንዲኖር አባት ማስገደድ እንደሌለበት ሠራተኛው ሲናገር፣ ነገር ግን ሁለቱም በደስታ አብረው የሚኖሩበትን መንገድ መፈለጉ መቻል ይኖርባቸዋል።

በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት በኋላ ቤተሰብና ሠራተኛው በመገናኘት ለቤተሰቡ ጥሩ ስለነበሩት በመነጋገር የስምምነት ውል ያደርጋሉ። አባት ልጁ በሚያደርጋቸው ነገሮች ላይ ደስተኛ አልነበረም፣ ነገር ግን ልጁ ከቤተሰቡ ጋር ለመኖርና ባደረጉት ስምምነት ውል መሰረት በመጽናቱ አባቱ ደስተኛ ነበር። ከዚያ በኋላ ምንም እንዳልተጨቃጨቁ ነው።

## ለወጣት ሠራተኛ ማነጋገር



የቤተሰብ አባል በወጣት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ላይ ለመሄድ ስለመፈቀዱ እርግጠኛ ካልሆኑ የወጣት ሠራተኛን ወይም ፕሮግራም አስተባባሪ ማነጋገር ይችላሉ። ብዙጊዜ የአገልግሎት፣ የፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ለማነጋገር ኃላፊነቱን የወሰደ የሠራተኛ ስምና የስልክ ቁጥር ይኖራል።

እንዲሁም አስተርጓሚ ካስፈለግዎ እንዲቀርብልዎ መጠየቅ ይችላሉ። አብዛኞቹ የወጣት ሠራተኞች የባለሙያ አስተርጓሚን አጠቃቀም ማወቅ ሲገባቸው እርስዎ በመረጡት ቋንቋ ለመነጋገር እንዲችሉ መብትዎ መጠበቅ አለበት። በተጨማሪም የወጣት ሠራተኞችን በሥራ ቦታቸው ላይ መጎብኘት ሲቻል ወይም በቤትዎ ወይም በመረጡት ቦታ ላይ መጥተው መጎብኘት ይችላሉ።

ሊጠይቁት ከሚፈልጉት ውስጥ ሊካተት የሚችል :

- ልጄ በምን እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ እንደሚችል?
- በቦታው ማን እንደሚገኝና ማን እንደሚቆጣጠራቸው?
- ስለደህንነታቸው እንዴት ማወቅ እችላለሁ?
- ልጄ የሚፈልገውን ነገር ማቅረብ ይችላሉን - እንደ የመጠለያ ቦታ ወይም የተለየ ምግብ አቅርቦት?
- ወደ እንቅስቃሴ ቦታውና ቤታቸው እንዴት መሄድና መመለስ ይችላሉ?

## ማጠቃለያ

በአውስትራሊያ ውስጥ ስለሚገኝ የወጣት ሠራተኞችና አገልግሎት የሥራ ድርሻና ጠቀሜታ በበለጠ ለማወቅ ይህ መረጃ እንደሚረዳ ተስፋ አለን። ወደ አውስትራሊያ የተሰደደ ማንኛውም ሰው አወንታዊና ደስታ የተሞላበት ሕይወት የመመስረት መብት ሲኖረው፣ እንዲሁም መደረግ ያለበትን የማካፈል እድል ይሰጣል። ቤተሰብ ይህንን ለማድረግ በወጣት ሠራተኞችና አገልግሎቶች በኩል እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

በጥራዝ ወረቀቱ ላይ ባለው ማንኛውም ነገር በበለጠ መርጃ ካስፈለግዎ ወይም አንዳንድ መረጃዎች ግልጽ ካልሆኑ የሚከተለውን ማነጋገር ይችላሉ :

- በአካባቢዎ ምክር ቤት ወይም አስተዳደር የሚገኙትን የወጣት ሠራተኛ ወይም የወጣት አገልግሎት
  www.youthcentral.vic.gov.au
- በሕብረ ባህላዊ የወጣት ጉዳዮች ማእከል/
  Centre for Multicultural Youth Issues
  www.cmyi.net.au
- ABCD አሳዳጊ ጎረምሳ/ኮረዳ Parenting Young Adolescents
  www.abcdparenting.org.au
- በአውስትራሊያ የቤተሰብ አገልግሎት/
  (Familiy Services Australia)
  www.fsa.org.au


© Centre for Multicultural Youth Issues 2006